ቀኙ መካከል የውል ግንኙነት እንደነበረ ስለሚያስረዳ በተጠሪ የተጠየቁትን ክፍያዎች አመልካች መክፈል አለበት በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 01741 ታህሣስ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የክልሉ የምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.12681 ጥር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል፡፡
2. ተጠሪ የአመልካች ተቀጣሪ ስላልነበሩ አመልካች በተጠሪ የተጠየቀውን ክፍያ ለመክፈል አይገደድም በማለት ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 29949

ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

ነ/ፈጅ አለሙ ዋሴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዋሲሁን አዳነ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀረብ የቻለው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠርና በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች የደረሱበት የደመወዝ ስኬል ላይ እንዲደርስ በማለት ውሣኔ በመስጠቱና በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ ውሣኔ በማጽናቱ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ ሂደትም ባጭሩ ሲታይ በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት የሠራበት የ65 ቀን ደመወዝና ብር 200 (ሁለት መቶ) ኪሣራ አመልካች ከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት በማለት ጥቅምት 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀም ሣይቀጥል እንደዚሁም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ተቀጥሮ እንዲሰራ ፍ/ቤቱ በተለያየ ጊዜ ውሣኔ መስጠቱን አመልካች ከሰበር አቤቱታው ጋር አያይዞ ያቀረባቸው የፍ/ቤቱ ውሣኔዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በዚህም መሠረት ኅዳር 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ በተገኘው ክፍት የሥራ ቦታ ተቀጥሮ እንዲሰራ፣

ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ደግሞ በአዋሽ በሚከፈተው የአመልካች የዲስትሪክት ቅርንጫፍ መ/ቤት በተገኘው ክፍት ቦታ ተጠሪ ተቀጥሮ እንዲሰራ

እንደዚሁም ነሐሴ 8 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአዋሽ የዲስትሪክት ጽ/ቤት በተገኘው ቦታ ተጠሪ ተቀጥሮ እንዲሰራ በማለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ መ/ቤት እንዲቀጠር በማለት ፍ/ቤቱ በሰጠው ተደጋጋሚ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ከታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀጠር የተደረገ ቢሆንም መቀጠር ከነበረብኝ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ መድረስ የሚገባኝ የደመወዝ ስኬል ላይ መድረስ ይገባኛል በማለት ተጠሪ ክርክር በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ይህንኑ የተጠሪን ክርክርን ተቀብሎ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠርና በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች የደረሱበት የደመወዝ ስኬል እንዲደርስ በማለት ጥር 1 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ ከ1990 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም በሥራ ላይ ያልነበረ መሆኑ እየታወቀ በሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅምና የደረጃ ዕድገት ይከፈለው የመባሉ አግባብነት ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ፍ/ቤቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ የሰበር አቤቱታው በአግባቡ የቀረበ እንዳልሆነ በመዘርዘር የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ተጠሪ ሥራ ላይ ባልነበረበት ጊዜ ሊደርስበት የሚገባው የደመወዝ ስኬል ተጠብቆለት



ደመወዝ እንዲከፈለው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ክርክር በፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ጥቅምት 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሰጠው ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ለተጠሪ የ65 ቀን ደመወዝ እንደዚሁም ብር 200 (ሁለት መቶ) ኪሣራ እንዲከፍልና ተጠሪም ከሥራ እንዲሰናበት በማለት ነው፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረትም ተጠሪ የአፈፃፀም አቤቱታውን አቅርቦ ፍ/ቤቱ በውሣኔው መሠረት አፈፃፀሙን መቀጠል ሲገባው በተለያየ ጊዜ ፍርድ ያላረፈበትን የአፈፃፀም ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ መ/ቤት ከታህሳስ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠር መደረጉን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ ሥራ እንዲቀጠር በመደረጉ ሣይሆን የደመወዝ ስኬል ተጠብቆለት ደመወዝ ይከፈለው ተብሎ በተወሰነው ላይ በመሆኑ ይህም የአፈፃፀም ትእዛዝ ሲታይ ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ ባልተወሰነበት ሁኔታ የተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድ ባላረፈበት ነገር የአፈፃፀም ትእዛዝ መስጠት ደግሞ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት (Serious procedural irregularity) ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ በፍርድ ባልተወሰነበት ሁኔታ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዳለ በመቁጠር በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ከደረሱበት የደመወዝ ስኬል እንዲደረስ ተደርጎ ደመወዝ እንዲከፈለው በማለት የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለው ከመሆኑም በላይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 54/1/ ላይ የተደነገገውንና ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ሥራ ነው የሚለውን የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡